MONTGOMERY COUNTY PUBLIC SCHOOLS
Maryland

# የእንግሊዘኛ ቋንቋ ስነጥበብ/ሊተርሲ፣ ሂሳብ፣ ሳይንስ እና የማህበራዊ ጥናት ፈተናዎች/ምዘናዎች MCAP የውጤት ሪፖርትን መረዳት

የሜሪላንድ አጠቃላይ የትምህርት ምዘና ፕሮግራም (MCAP) የእንግሊዘኛ ቋንቋ ስነጥበብ/ሊተርሲ፣ ሂሳብ፣ ሳይንስ (5ኛ ክፍል ወይም 8ኛ ክፍል) እና ማህበራዊ ጥናት/ሶሻል ስተዲ - 8ኛ ክፍል ከሜሪላንድ የኮሌጅ እና የስራ ዝግጁነት የትምህርት ምዘናዎች የተሰጡት 2023 2024 የትምህርት ዓመት በስፕሪንግ ወቅት ነው። ለርስዎ ተማሪ ከሚሰጡት የትምህርት አፈጻጸም ምዘናዎች ይሄኛው አንዱ መለኪያ ነው። በምዘናዎቹ የተገኙት ውጤቶች ተማሪዎን ለሚያስተምሩ መምህራን፣ ለት/ቤቱ እና ለትምህርት ስርአቱ ስለ አካዳሚክ አፈጻፀም መረጃ ይሰጣል፥ እና ለእርስዎም ስለ ተማሪዎ የትምህርት ብቃት ደረጃ የተወሰነ ግንዛቤ ይሰጥዎታል። ተማሪ የአካዳሚክ ደረጃዎችን ለማሟላት የሚያደርገውን/የምታደርገውን ጥረት ግልፅ ለማድረግ MCAP ውጤቶች ከተማሪው(ዋ) የትምህርት ክፍል አፈጻጸም፣ በሪፖርት ካርድ ላይ የተመዘገቡ ውጤቶች፣ እና የአስተማሪ ግምገማ ጋር መገናዘብ አለበት።

## የእርስዎን ተማሪ የውጤት ሪፖርት እንዴት እንደሚያነቡ

1. **አጠቃላይ ክንውን/አፈጻጸም**–ተማሪዎች አጠቃላይ ውጤት የሚያገኙት ከአራቱ የትምህርት አፈጻፀም ደረጃዎች በአንዱ ላይ በሚመደበው በእያንዳንዱ የትምህርት አይነት ተመስርቶ ነው።  የአፈጻጸም ደረጃዎች፡ተማሪው(ዋ) የትምህርት ብቃት ደረጃን ገና እንዳላሳየ(ች) ከሚያመለክተው ከደረጃ 1 እስከ ክፍል ደረጃ መመዘኛዎችን የላቀ የትምህርት ብቃት እንዳሳየ(ች) የሚያመለክት ደረጃ 4 ድረስ ይለያያሉ።

2. **የውጤት ደረጃ** – ይህ ሚዛን የእያንዳንዱን ክንውን የውጤት ደረጃ እና የእርስዎ ተማሪ ከእነዚህ መካከል በየትኛው ደረጃ እንደሚገኝ/እንደምትገኝ ያመለክታል።

3. **ለኮሌጅ እና የሙያ ሥራ ዝግጁ**– 3 ወይም 4 ነጥብ ያገኙ ተማሪዎች የሚጠበቅባቸውን የክፍል ደረጃ አሟልተዋል ወይም ከማሟላትም የሚበልጥ ስለሆነ ከሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት እንደተመረቁ የኮሌጅ ደረጃ ኮርስ ለመውሰድ ዝግጁ ናቸው።

4. **አጠቃላይ የውጤት እርከን ማነፃፀሪያ**–ይሄኛው ክፍል የሚያሳየው በተመሣሣይ የክፍል ደረጃ፣ በተመሣሣይ ት/ቤት፣ በአጠቃላይ በትምህርት ዲስትሪክቱ ዙርያ፣ እና በስቴቱ ውስጥ ከሌሎቹ ተማሪዎች ጋር ሲመዛዘን የእርስዎ ልጅ እንዴት እያከናወነ(ች) እንደሆነ ያመለክታል።



# የተማሪዎን የውጤት ሪፖርት እንዴት እንደሚያነቡ (የቀጠለ ....)

**5. የማንበብ/የመጻፍ ክንዋኔ** – የእንግሊዝኛ ቋንቋ ስነጥበብ/ሊተርሲ ሪፖርት የእርስዎን ተማሪ የማንበብ እና የመጻፍ ነጥቦችን ያነፃጽራል። በዚህ ንዑስ ክፍል በሚገኙ ጥያቄዎች ተማሪዎ ያስመዘገበ(ች)ውን ውጤት በቁጥር ያመለክታል። ለማጣቀሻ ያህል ተማሪዎ ካስገኘ(ች)ው ግላዊ ውጤት በተጨማሪ የውጤት "ከ-እስከ" ገደብ ተገልጿል። ይህኛው ን/ክፍል የት/ቤቱን፣ የዲስትሪክቱን፣ እና የስቴቱን አማካይ ውጤቶች በተጨማሪ ያካትታል።

**6. የውጤት ዝርዝር**– የውጤት ሪፖርት በተወሰነ የክህሎት ደረጃ የእርስዎ ልጅ እያቀላጠፈ(ች) ያለውን ወይም ማሻሻል ያለበ(ባ)ትን የተማሪዎን የአፈጻጸም ዝርዝር ያመለክታል። እያንዳንዱ ዝርዝር የሚጠበቅባቸውን ካሟሉ ተማሪዎች ጋር የእርስዎን ተማሪ አፈጻጸም የሚያሣይ ክብ ማነጻፀሪያ ያካትታል። የሚማርበትን/የምትማርበትን ክፍል የብቃት/የክሂሎት ግንዛቤ ደረጃ የሚገልጽ ውጤት-የሚያሳይ ገለፃም በተጨማሪ ተካትቷል።







## ስለ ሜሪላንድ አጠቃላይ ምዘና እና ፈተና - እውነታ

- ✓ ከ3ኛ እስከ 8ኛ ክፍል ተማሪዎች ወደ ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት ከገቡ በኋላ ዓመታዊ ስቴት አቀፍ መመዘኛ እንዲወስዱ የፌደራል ህግ ይደነግጋል።
- ✓ የሜሪላንድ የትምህርት ባለሙያዎች ከትንታኔ አንስቶ ትክክለኛነታቸውን እስከ መገምገም ድረስ እያንዳንዱን ፈተና በማዘጋጀት እና በማሻሻል ከፍተኛ ተሳትፎ ያደርጋሉ።
- ✓ የአካል ጉዳተኝነት ያላቸው ተማሪዎች ሊፈቀድላቸው ስለሚችል መገልገያዎች እና አኮሞዴሽን ለመወያየት በልጆቻቸው IEP ወይም 504 ቡድን አማካይነት ለወላጆቻቸው ሊገለጽላቸዉ ይገባል።
- ✓ በትምህርት አመቱ መጨረሻ የሚሰጡ የትምህርት ውጤቶች የተማሪን የክፍል ደረጃ ትምህርት የግንዛቤ ደረጃ ያመለክታሉ።
- ✓ የውጤት ሪፖርቶች የሚያገለግሎት፡- መመህራን የዳበረ የማስተማር እቅድ አዘጋጅተው ተማሪዎችን ለመጪው የትምህርት ዘመን የሚቀጥለውን እርከን እቅድ ለማዘጋጀት የሚረዱ መሳርያዎች ናቸው።
- ✓ ቤተሰቦች ስለልጃቸው አካዴሚያዊ ጥንካሬና መሻሻል ስላለበት ሁኔታ ከልጃቸው መምህራንና የት/ቤት ሃላፊዎች ጋር ውይይት ለማድረግ እነዚህን ውጤቶች መጠቀም ይችላሉ።
- ✓ በት/ቤትም ሆነ በመኖርያ ቤት የተማሪው(ዋ)ን የትምህርት ፍላጎት በይበልጥ እንዴት መደገፍ እንደሚቻል እያንዳንዱን ጉዳይ አብሮ መወሰን ይቻላል።

## ከዚህ በታች የሚገኙት ጠቃሚ ድረ-ገጾች ስለሆኑ ይጎብኟቸው!

- ✓ **MCAP የመልመጃ ፈተናዎች/Practice Tests** - support.mdassessments.com
- ✓ **ስኬት/Achieve** - Resources on Standards – achieve.org
- ✓ **የሜሪላንድ ስቴት የትምህርት መምሪያ/MD State Dept of Education** - marylandpublicschools.org
- ✓ **የሚደነቁ ልጆች/Great Kids** - greatschools.org/gk/common-core-test-guide
- ✓ **ጀግና ተማሪ ሁን(ኚ)/Be a Learning Hero** - bealearninghero.org/learning-tools/skill-builder